ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

ፀረ-ሙስና ቅጽ 2 ቁጥር 22 ሀምሌ 15/2017 ዓ.ም

## በውስጥ ገጾች

ከፓስፖርት አገልግሎት ጋር ተያይዞ ብልሹ አሰራር ውስጥ የገቡ 26 ሰራተኞች በህግ ተጠያቂ ተደረጉ
ገጽ 2

የሌብነትና ብልሹ አሰራር ተግባር በፈጸሙ 4 ሺህ 965 ሰዎች ላይ ርምጃ ተወስዷል- ክብርት አዳነች አቤቤ
ገጽ 3

በክልሉ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ከ224 ሚሊዮን ብር በላይ ከምዝበራ ማዳን ተችሏል
ገጽ 3

## ኮሚሽኑ የሙስና መከላከል ጥናት አሰራር ሥርዓት እና የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት እንዲሁም ተገቢነት ማረጋገጫ ፕሮቶኮል አዘጋጅቶ ተግባራዊ እንዲሆን ወሰነ







የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዘርፍ-ተኮር የሙስና መከላከል ጥናት በማካሄድ ለተቋማት መሪዎች ምክረ-ሐሳብ የማቅረብ እና አግባብነት ያላቸው የሪፎርም ሥራዎች እንዲሰሩ ድጋፍ እየሰጠ ይገኛል።

በዚህ ተልዕኮ፣ በርካታ ተቋማት መሪዎች የጥናቱን ምክረ-ሐሳብ ሥራ ላይ እያዋሉ እና የአሰራር ሥርዓት ግልጽነት እና ተጠያቂነት የማጎልበት ተግባር እያከናወኑ መሆኑን በዚህ በጀት ዓመት በተደረገው ክትትል አረጋግጧል።

በዚህ ዓመት በአገርዓቀፍ ደረጃ የሙስና መከላከል ሥራ በቀጣይ ለማካሄድ የተቋማትን የአሰራር ሥርዓት ችግሮችን የሚፈትሹ 127 ጥናቶች ተካሂደዋል። በጥናቶች ግኝት መሠረት፣ የፀረሙስና ትግል የሚያጠናክሩ ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናል።

በመሆኑም፣ ኮሚሽኑ የሙስና መከላከል ጥናት ሥራ እና የትግበራ ውጤታማነት ክትትል ሥራ ይበልጥ በመርህ ላይ የተመሠረተ ለማድረግ የጥናት አሰራር ሥርዓት እና የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት እንዲሁም ተገቢነት ማረጋገጫ ፕሮቶኮል አዘጋጅቶ ሥራ ላይ እንዲውል ወስኗል።

## የኮሚሽኑ አመራርና ሰራተኞች የችግኝ ተከላ መርሐግብር አካሄዱ

አረንጓዴ አሻራ
GREEN LEGACY





የፌደራል የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራር እና ሰራተኞች፣ ካራ አዲስ አበባ ፖሊስ ግቢ የአረንጓደ አሻራ መርሐግብር ሀምሌ 9/2017 ዓ.ም አካሂደዋል። በዕለቱ መርሐግብሩን ያስጀመሩት የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ፒኤችዲ) መልካም ነገሮችን በመትከል እንደ ሀገር ማንሰራራት እንደሚቻል በፕሮግራሙ ወቅት ገልጸል፡፡

# የደቡብ አፍሪካ የፖሊስ ሚኒስትር በሙስና እና በተደራጀ የወንጀል ድርጊት ተጠርጥረው ከስልጣን ታገዱ

የደቡብ አፍሪካ ፕሬዚዳንት ሲሪል ራማፎሳ፤ ከተደራጀ የወንጀል ድርጊት ጋር ግንኙነት አላቸው የሚል ውንጀላ የቀረበባቸውን የአገሪቱን የፖሊስ ሚኒስትር ሴንዞ ሙቹኑን በአስቸኳይ "እረፍት" ማስወጣታቸው ተዘግቧል።

ራማፎሳ፤ እሁድ ዕለት በቴሌቪዥን ቀጥታ በተላለፈ እና ለአገሪቱ ዜጎች ባደረጉት ንግግር፤ ክሶቹን ሕገ መንግሥቱን የሚያዳክሙ እና ብሔራዊ ደህንነትን አደጋ ላይ የሚጥሉ ሲሉ የገለጿቸው ሲሆን ጉዳዩ በፍትህ ኮሚሽን እንደሚታይ አስታውቀዋል።




የሕግ ፕሮፌሰር የሆኑ ፊሮዝ ካቻሊያ ጊዜያዊ የፖሊስ ሚኒስትር ሆነው መሾማቸውንም ይፋ አድርገዋል።

ሙቹኑ በበኩላቸው ምንም ዓይነት ጥፋት አለመፈጸማቸውን በመግለጽ "ለቀረቡባቸው ክሶች ምላሽ ለመስጠት ዝግጁ ነኝ" ብለዋል።

በሙቹኑ ላይ ከቀረቡት ክሶች መካከል የፖለቲካዊ ግድያዎች በተመለከቱ ምርመራዎች ውስጥ ጣልቃ መግባትን እና ከሕግ አስፈጻሚ ኤጀንሲዎች ጋር የተያያዙ የሙስና ድርጊቶች ይገኙበታል።

ፕሬዚዳንቱ በትናንቱ ንግግራቸው፤ በሙቹኑ ላይ የቀረቡት ክሶች "አስቸኳይ እና አጠቃላይ ምርመራን እንዲደረግ" ጥሪ አቅርበዋል።

በአገሪቱ ምክትል ዋና ዳኛ የሚመራው የፍትህ ኮሚሽን ሁሉንም ውንጀላዎች እንደሚመረምር ተናግረዋል፡፡

የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት
IMMIGRATION AND CITIZENSHIP SERVICE

## ከፓስፖርት አገልግሎት ጋር ተያይዞ ብልሹ አሰራር ውስጥ የገቡ 26 ሰራተኞች በህግ ተጠያቂ ተደረጉ

ከፓስፖርት አገልግሎት ጋር ተያይዞ ብልሹ አሰራር ውስጥ የገቡ 26 ሰራተኞች በህግ ተጠያቂ መደረጋቸውን የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት አስታወቀ።

አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ችግር የሚፈጥሩ፤ የማጭበርበርና የማታለል ተግባር፣ በህገ-ወጥ መንገድ በኦንላይን አስቸኳይ ፓስፖርት የሚሞሉ 231 ተጠርጣሪዎች በህግ ቁጥጥር ስር ዉለዋል መዋላቸውም ተገልጿል።

3,868 ግለሰቦች የተጭበረበረ ሰነድ በመጠቀም ፓስፖርት ሊያወጡ ሲሞክሩ በህግ እንዲጠየቁ ተደርጓል።

በተጨማሪም 12,127 የውጭ ዜጎች ሃሰተኛ ሰነዶችን በመያዝ በህገ ወጥ መንገድ ሲንቀሳቀሱ ተይዘው አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰድባቸው መደረጉን አገልግሎቱ አስታውቋል።










## የሌብነትና ብልሹ አሰራር ተግባር በፈጸሙ 4 ሺህ 965 ሰዎች ላይ ርምጃ ተወስዷል-ክብርት አዳነች አቤቤ

በጀት ዓመት የሌብነትና ብልሹ አሰራር ተግባር በፈጸሙ አራት ሺህ 965 ሰዎች ላይ ህጋዊና አስተዳደራዊ ርምጃ ተወስዷል ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገለጹ።

በ3ኛው የአዲስ አበባ ምክር ቤት 4ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 4ኛ መደበኛ ጉባዔ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ የ2017 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም እና የ2018 በጀት ዓመት የትኩረት አቅጣጫን አቅርበዋል።

ከንቲባዋ የተቋም ግንባታና አገልግሎት አሰጣጥን በሚመለከት እንደገለጹት፤ የሌብነትና ብልሹ አሰራር ተግባር በፈጸሙ 4 ሽህ 965 አመራሮችን፣ ፈጻሚዎችን እና ተገልጋዮችን ተጠያቂ በማድረግ ህጋዊ እና አስተዳደራዊ ርምጃዎች መወሰዱን ገልፀዋል።

አገልግሎቶችን ዲጂታላይዝ ከማድረግ አንጻርም በርካታ ስራዎች መሰራታቸውን አመላክተዋል።





## በክልሉ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ከ224 ሚሊዮን ብር በላይ ከምዝበራ ማዳን ተችሏል




በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል በተጠናቀቀው በጀት ዓመት በተከናወነ ሙስናን የመከላከል ስራ ከ224 ሚሊዮን ብር በላይ የመንግሥትና የህዝብ ሃብት ከምዝበራ ማዳንና ማስመለስ መቻሉን የክልሉ የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ገለጸ። በበጀት ዓመቱ በክልሉ 4 ሺህ 200 የመንግስት ሰራተኞችን በመመዝገብ የምስክር ወረቀት መሰጠቱም ተገልጿል። የክልሉ ስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሙሉሰው ዘውዴ እንደገለፁት፣ በዓመቱ 729 ጥቆማዎችን በጽሁፍ፣ በስልክ፣ በአካልና በተለያዩ የመረጃ መቀበያ አማራጮች መቀበሉን ጠቁመዋል።

ከቀረቡት ጥቆማዎች ውስጥ 292ቱ በአስቸኳይ ሙስና መከላከል እንዲሁም 124ቱ ላይ ማስረጃን በማደራጀትና በመተንተን ለፍትሕ አካላት የማስተላለፍ ስራ ተሰርቷል ብለዋል። 292 ጥቆማዎች ላይ በተሰራው አስቸኳይ የሙስና መከላከል ስራ ሊመዘበር የነበረን ከ178 ሚሊዮን 871 ሺህ ብር በላይ ማዳን መቻሉን ኮሚሽነር ሙሉሰው ተናግረዋል።

እንደ ኮሚሽነር ሙሉሰው ገለጻ፥ ከገንዘብ በተጨማሪ ከ166 ሺህ 708 ካሬ የከተማ እንዲሁም ከ505 ሄክታር በላይ የገጠር መሬት ማዳን ተችሏል። በኦዲት ግኝት ተመዝብሮ የነበረን ሀብት ለማስመለስ በተደረገው ጥረትም ከ45 ሚሊዮን 618 ሺህ ብር በላይ እንዲሁም በዓይነት የተለያዩ የመንግስት ንብረትና ቁሳቁሶችን የማስመለስ ስራ መሰራቱን ገልፀዋል።

ይህም በአጠቃላይ በተሰራው ሙስናን የመከላከል ስራ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ከ224 ሚሊዮን 489 ሺህ ብር በላይ በገንዘብና በዓይነት የመንግሥትና የህዝብ ሃብትን ከምዝበራ ማዳንና ማስመለስ መቻሉን ነው የገለጹት። በተጨማሪም በተገባደደው በጀት ዓመት 4 ሺህ 200 የመንግስት ሰራተኞችን በመመዝገብ የምስክር ወረቀት መሰጠቱን ጠቁመው፥ የመረጃውን ትክክለኛነት በማረጋገጥ ግልፀኝነትና ተጠያቂነትን የማስፈን ስራ እየተሰራ መሆኑንም ተናግረዋል።

የኮሚሽኑን የአሰራር ስርዓት ከማሻሻልና ብቃት ከማሳደግ አኳያ በተሰሩ ስራዎች ሶስት የተለያዩ ሕጎችን በማዘጋጀት ወደ ስራ እንዲገቡ መደረጉን ኮሚሽነሩ ገልጸዋል፡፡




www.feacc.gov.et | www.facebook.com/feaccOfficial | t.me/feacc

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

## በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

ስልክ 011552-77-79
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission
ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች
www.feaccdars.gov.et

## ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች

ስልክ 011552-77-92/ 011553-38-52
ሞባይል 0935947533
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ኢ-ሜይል CorruptionReportEthiopia@feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስኣፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1

# ርዕሰ -አንቀፅ

## ሚዲያዎች በፀረ-ሙስና ትግል ሀገራዊና ተቋማዊ ግዴታቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል

ሚዲያዎች፣ በፀረሙስና ትግል ውስጥ ሚናቸውን መወጣት እንዲችሉ፣ አስቀድመው ስለሙስና ምንነት ሊያውቁ ይገባል። ሚዲያዎች ሙስናን ለመከላከል የሚሠሩት ሥራ ዕውቀትን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት። ያኔ የፀረሙስና ትግሉን በከፍተኛ ሁኔታ ያግዙታል። የሚዲያ ባለሙያዎች የሙስና ምንነትን፣ መንስኤና የሚያስከትለውን ጉዳት እንዲሁም ስለመከላከያ መንገዶቹ በውል መገንዘባቸው፣ የኅብረተሰብን አመለካከት ለመቀየር፣ በመንግሥት አሠራር ላይ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ያሰፈነ አሠራር እንዲዘረጋ ለማድረግ የሚያስችሉ ሥራዎችን ለመሥራት ያስችላቸዋል። በዚህ ሁኔታ ከጠነከሩ፣ በፀረ ሙስና ትግሉ፣ ልዩ ልዩ ፕሮግራሞችን በመሥራትና ዘገባዎችንና ዜናዎችን በብቃት በማሰራጨት፣ ዜጎች የፀረሙስና ትግሉ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ ቁርጠኝነት ያሳያሉ።

ባንጻሩም፣ የሚዲያ ባለሙያዎች የሙስናን ጠንቀኝነት በውል ካልተገነዘቡ፣ ለፀረ ሙስና ትግሉ የሚሰጡት ትኩረት ዝቅተኛ ይሆናል። በፀረሙስና ትግሉ ላይም የሚጠበቅባቸውን ሚና በአግባቡ አይወጡም። ሚዲያ በአግባቡ ሚናውን አልተወጣም ማለት፣ የሙስናን ገመና የሚያጋልጡ ተግባራት ተሰናከሉ ማለት ነው። የማጋለጡ ተግባር በተሰናከለ ቁጥር ደግሞ፣ ይህ ጠንቀኛ ወንጀል እየፈረጠመና እየተስፋፋ መሔዱ አለ የማይባል ሐቅ ይሆናል፡፡

በመሆኑም የሚዲያ ተቋማት ትክክለኛ ታማኝ መረጃዎችን በማስተላለፍ የሥነምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል ሥራዎች በመስራት በአየር ሰዓት፣ በተቋም ድረ-ገፅ፣ በማህበራዊ ሚዲያና በህትመት ዘዴዎች በመታገዝ ህብረተሰቡ ጋር እንዲደርስ በማድረግ ሀገራዊና ተቋማዊ ግዴታቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡





# አገራዊ የተቋማት የሥነምግባር መከታተያ አደረጃጀት ማስፋት እና ማብቃት

| ተ.ቁ | ተቋም | የተደራጀ ስነምግባር መከታተያ የሰው ኃይል ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር |
| 1 | የፌደራል የሥነምግር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 832 | 326 | 1158 |
| 2 | የኦሮሚያ ክልል የሥነምግር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 1895 | 1159 | 3054 |
| 3 | የሲዳማ ክልል የሥነምግር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 512 | 66 | 578 |
| 4 | የቤ/ጉሙዝ ክልል የሥነምግር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 85 | 20 | 105 |
| 5 | የአማራ ክልል የሥነምግር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 236 | 77 | 317 |
| 6 | የማ/ኢትዮጵያ ክልል የሥነምግር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 889 | 207 | 1096 |
| 7 | የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የሥነምግር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 845 | 157 | 1,002 |
| 8 | የደ/ም/ኢትዮጵያ ክልል የሥነምግር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 132 | 21 | 153 |
| 9 | የትግራይ ክልል የሥነምግር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 875 | 294 | 1169 |
| 10 | የአዲስ አበባ ከተማ የሥነምግር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 332 | 292 | 624 |
| 11 | የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የሥነምግር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 1 | 2 | 3 |
| 12 | የሱማሌ ክልል የሥነምግር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 388 | 157 | 545 |
| 13 | የጋምቤላ ክልል የሥነምግር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 65 | 6 | 71 |
| 14 | የሀረሪ ክልል የሥነምግር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 18 | 36 | 54 |
| 15 | የአፋር ክልል የሥነምግር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 111 | 65 | 176 |
| | አጠቃላይ | 7235 | 2884 | 10,123 |

ለጥቆማ!

**NCRS** ሞባይል መተግበሪያ

ይጠቀሙ!



## በ20 17 በጀት ዓመት አገራዊ የትዉልድ ሥነምግባር እና ሙስና መከላከል አቅም ግንባታ ሥልጠና አፈጻፀም

| ተ.ቁ | ኮሚሽን | 2017 በጀት አፈፃፀም |
|---|---|---|
| 1. | የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 75,676 |
| 2. | የትግራይ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 375 |
| 3. | የአፋር ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 550 |
| 4. | የአማራ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 9084 |
| 5. | የሲዳማ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 4379 |
| 6. | የኦሮሚያ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 35470 |
| 7. | የደቡብ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 290 |
| 8. | ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 3029 |
| 9. | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 142,210 |
| 10. | የጋምቤላ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 2995 |
| 11. | የሶማሌ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 1430 |
| 12. | የቤኒሻንጉል ጉሙዝ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 5153 |
| 13. | የአዲስ አበባ ከተማ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 162,420 |
| 14. | የሀረሪ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 736 |
| 15. | የድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 1,577 |
| | ድምር | 445,374 |

## አገራዊ የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ሥራ አፈጻጸም

| ተ.ቁ | ተቋም | በማጣራት ሥራ ብዛት | የዳነ ሀብት በብር | የዳነ በሀብት በአይነት |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 24 | 152,997,050.00 | - |
| 2. | የኦሮሚያ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 99 | 564,705,890.30 | 7,300 ካ.ሜ የከተማ 2.5 ሄ/ር የገጠር መሬት |
| 3. | የአማራ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 73 | 43,345,100.00 | 4,155.68 ካ.ሜ |
| 4. | የአዲስ አበባ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 169 | 684,328,185.28 | 5,570.19 ካ.ሬ |
| 5. | የሶማሌ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 5 | 47,217,632 | 10,583 ካ.ሜ የከተማ እና 160 ሄ/ር የገጠር መሬት |
| 6. | የሐረሪ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 9 | 6,775,437 | 160 ካ. ሜ |
| 7. | የሲዳማ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 46 | 24,157,529.47 | 14,165 ካ.ሜ የከተማ እና 62.317 ሄ/ር የገጠር መሬት |
| 8. | የቤ/ጉ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 8 | 1,142.543.00 | - |
| 9. | የደቡብ ም/ኢትዮጵያ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 292 | 178,871,392.2 | 166,708.55 ካ.ሜ ከተማ እና 505.68 ሄ/ር ገጠር መሬት |
| 10. | የጋምቤላ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 8 | 5,649,888.88 | - |
| 11. | የትግራይ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 4 | 27,000,000.00 | - |
| 12. | የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 16 | 382,628,573.41 | - |
| 13. | የማዕካለዊ ኢ/ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 822 | 137,020,988.25 | 44,815.73 ካ.ሜ የከተማ እና 930.6 ሄ/ር የገጠር መሬት |
| 14. | የድሬዳዋ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 2 | 345,000.00 | 17 ካ.ሜ መሬት |
| 15. | የአፋር ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 6 | - | - |





## ቆይታ

# ሙስናና ብልሹ አሰራር የሁሉንም ዜጋ ህወት የሚነካ ጉዳይ ነው፡፡

### የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የስነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ም/ኮሚሽነርና ሙስናና ብልሹ አሰራር መከላከል ዘርፍ ኃላፊ

ዳግም ዳኔኤል

የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ተልዕኮውን ለመወጣት በተለያዩ አግባቦች ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡ የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ስራዎችን ከሚሰራባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሲሆን በዚህም በሁለት ሳምንት አንድ ጊዜ የሚዘጋጅ ዲጅታል ጋዜጣ በማዘጋጀት ለማህበረሰቡ ያደርሳል፡፡ ጋዜጣው ከያዛቸው አምዕዶች ውስጥ ቆይታ አንዱ ሲሆን በዚህ ወር ዝግጅት ቆይታ ያደረገው የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር ጋር ሲሆን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡



**ፀረ-ሙስና፡- ስምዎትንና የስራ ድርሻዎትን ለአንባቢያን ቢያስተዋውቁልን?**

ም/ኮሚሽነር ዳኔል ዳግም፡- ስሜ ም/ኮሚሽነር ዳግም ዳኔኤል አባላለሁ፡፡ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የስነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ም/ኮሚሽነርና ሙስናና ብልሹ አሰራር መከላከል ዘርፍ ኃላፊ ነኝ፡፡

**ፀረ-ሙስና፡- በተቋማችሁ በ2017 በጀት አመት ምን ምን ስራዎች ተሰሩ?**

ም/ኮሚሽነር ዳግም ዳኔኤል ፡- በበጀት አመቱ በክልል ደረጃ ኮሚሽናችን በዋነኛነት ዘጠኝ ዋና ዋና ግቦችን አስቀምጦ እነዚህ ዘጠኝ ዋና ዋና ግቦች ስር በርካታ ተግባራትንና ስራዎችን ሲሰራ ቆይቷል፡፡

የትውልድ ስነምግባር ግንባታ ጎን ለጎን የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ስራና የሀብት ምዝገባ ስራ እንዲሁም የሀብት ትክክለኝነት ማጣራት ስራዎችን በአመቱ መጀመሪያ አቅደን ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ ሰፊ ስራዎችን ስንሰራ ቆይተናል፡፡

**ፀረ-ሙስና፡- በአመቱ የተሰሩ ስራዎች በቁጥር መግለጽ ከተቻለ ቢገልጹልን?**

ም/ኮሚሽነር ዳኔኤል፡- በአስቸኳይ ሙስና መከላከል ስራ ስንሰራ በአመቱ የአቀድነው እቅድ መቶ ፐርሰንት የሚመጡ ጥቆማዎችን ለመቀበል አስቀምጠን ተንቀሳቅሰናል፡፡ በዚህ ረገድ በዚህ በጀት አመት 729 ጥቆማዎች በተለያየ ቻናል ቀርበዋል፡፡ ከቀረቡት ጥቆማዎች ውስጥ 292 የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ጥናት ተሰርቶባቸውዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ 124 የሚሆኑ ጥቆማዎች ተቀብለን ተንትነን ስናይ የሙስና ወንጀል ሊያቋቁም የሚችል፣ የሙስና አይነት ያላቸው መሆኑ በኮሚሽናችን ከተረጋገጠ በኋላ እነዚህ ጉዳዮች ለሚመለከታቸው የምርመራና የመክሰስ ስልጣን ላለው የፍትህ አካላት ልከናል፡፡ መላክ ብቻ ሳይሆን ጉዳዩን ክትትል ጭምር እያደረግን ያለንበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ በዚህ ሂደት እንግዲህ በአስቸኳይ የሙስና መከላከል ስራ ከሰራነው በዚህ በጀት አመት አጠቃላይ አንድ መቶ ሰባስምት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሰባአንድ ሺህ ሶስት መቶ ዘጠና ሁለት(178,871,392) ብር በጥሬ ገንዘብ ማዳን ተችሏል፡፡

በአይነት የተመለሱትን ስንመለከት ደግሞ በመሬት ዙሪያ ትኩረት ሰጠን ትልቅ የብልሽት በአብዛኛው ጥቆማዎች የሚያጠነጥኑት በመሬት ዙሪያ ላይ ስለነበረ እኛም ትኩረት አድርገን ጉዳዩን በመስራታችን በዚህ በጀት አመት አንድ መቶ አምሳስድስት ሺህ ሰባት መቶ ስምንት(156,708) ካሬ ሜትር የከተማ መሬት፣ አምስት መቶ አምስት(505) ሄክታር የገጠር መሬት በአስቸኳይ ሙስና መከላከል ማዳን ችለናል፡፡ በዚህ ሂደት የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ስራ በአይነትና በገንዘብ ያዳነውን፣ ሳይመዘበር እንዲድን ያደረግነውን እንደተጠበቀ ሆኖ በኦዲት የተመዘበረና በኦዲት ከተመዘበረ በኋላ በኦዲት የተረጋገጠን ሀብት የማስመለስ ስራ እንዲሁም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅተን በሰራነው ስራ በዚህ በጀት አመት ከአርባ አምስት ሚሊዮን ብር በላይ ተመዝብሮ የነበረ ሀብት የማስመለስ ስራ ተሰርቷል፡፡

**ፀረ-ሙስና፡- ከሙስናና ብልሹ አሰራርን ከመከላከል በተጨማሪ በትውልድ ስነምግባር ግንባታ ምን ምን ተግባራትን አከናወናችሁ?**

ም/ኮሚሽነር ዳግም ዳኔኤል፡- ብልሹ አሳራርና ሙስናን ከመከላከል ስራ ስንሰራ በአይነት፣ በገንዘብ የዳነ የተመለሰ ገንዘብ እንደተጠበቀ ሆኖ በአስቸኳይ ሙስና መከላከል ስራችን ብቻም ሳይሆን ከዛው ጎን ለጎን የትውልድ ስነምግባር ግንባታ ስራችንንም አያይዘን ሰርተናል፡፡ ከዚህ አንጻር በትውልድ ስነምግባር ግንባታ፣ በግንዛቤ ስራ የሰራናቸው ስራዎች አሉ፡፡ በዚህ ሂደት በዚህ በጀት አመት በዘርፉ ሁለት የስልጠና ሞጁሎችን አዘጋጅተናል፡፡ የስልጠና ሞጁሎችን ማዘጋጀት ብቻም ሳይሆን የግንዛቤ ስራዎችን ሰፊ እቅድ አቅደን በሰፊው መስራት እንዳለብን በእቅድ ከተግባባን በኋላ በዚህ አመት ብቻ ለአንድ መቶ አራት ሺህ ዘጠና ሰባት (104,097) ለሚሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ሰርተናል፡፡

የግንዛቤ ስራ ስንሰራ እንደትልቅ አቅም የተጠቀምነውና ትልቅ የንቅናቄ መድረኮችን ለግንዛቤ መድረኮችን እንድንጠቀም ያደረገን አለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን ሲከበር ከክልል ጀምሮ አስከታች አስከቀበሌ ድረስ፣ አስከት/ቤቶች ድረስ ሰፊ ንቅናቄ ስላለ የአለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀንን መነሻ አድረገን የሰራነው ስራ በንቅናቄው አብዛኛውን የማህበረሰብ ክፍል ተደራሽ እንድንሆንና እንድናደረግ ጥሩ አድል ፈጥሮልናል፡፡ ይሄን ከባለፈው አመት የቤት ስራ ወስደን ቀጣይ በሚኖርን ስራም ይሄን መድረክ፣ የንቅናቄ መድረኮችን እንደጥሩ አጋጣሚ ከተጠቀምን አብዛኛውን ማህበረሰብ በግንዛቤ ተደራሽ የመሆን አድል ስላለ ት/ት የወሰድንበት ነው፡፡

ከግንዛቤ ስራ ጎን ለጎን ስልጠና ነው በተለይ አብዛኛው ጊዜ ስልጠናን ለተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ይሰጣል፣ ግን ደግሞ እኛ በዚህ አመት ትኩረት ያደረግነው ከፍተኛ አመራሩን ነው፣ ስልጠና ከወሰደ በስሩ የሚመራቸው፣ የሚስተባብራቸው በርካታ አመራሮች፣ ሰራተኞች በስሩ ስላሉ አንድ መቶ አርባስምንት የሚሆኑ የክልል ከፍተኛ አመራሮች ስልጠና ሰጠናል፡፡ በዚህ ብቻ ሳናበቃ በተለይ የትውልድ ስነምግባር ግንባታን ስራ ሲሰራ ዋናው ማእከል አድርገን መስራት ያለብን ታዳጊዎችንና ወጣቶችን ያገናዘበ መሆን አለበት፡፡ ታዳጊዎችንና ወጣቶችን ማግኘት የሚቻለው ደግሞ ት/ቤት ላይ ነው፡፡ ስለዚህ ትኩረት አድርገን የሰራነው በክልላችን የሚገኙ ከፍተኛ ሁለተኛ ት/ቤቶች አሉ፣ እነዛ ውስጥ የሚገኙ ወደ ሰማንያ ሁለት (82) ክበባት አሉ፡፡ በትውልድ ስነምግባር ግንባታ ላይ የታዳጊዎች የወጣቶች ሚና ምን መሆን አለበት የሚለውን ክበባትን ማጠናከር ብቻ ሳይሆን ክበባትን እንደምቹ ሁኔታ ተጠቅመን ግንዛቤ የፈጠርንበት ታዳጊዎችን ተደራሽ ሆነናል፡፡ በዚህ በ182 ክበባት ውስጥ ወደ ሃያ አንድ ሺህ አራት መቶ ሀምሳ ሁለት (21,452) ለሚሆኑ ታዳጊዎችና ወጣቶች ግንዛቤ የፈጠርንበት፣ ታዳጊዎችን ወጣቶችን ያገኘንበት ስራ የተከናወነበት ሁኔታ ፈጥረናል፡፡

በተለይ በ2017 ዓ.ም በያዝነው በጀት አመት እንደጥሩ ስራ ብለን የወሰድነው አንዱ በተለይ ህዝቡን በብዛት የሚያማርሩ ብልሹ አሰራሮች ያሉበትን ቦታዎች ለይተን የአሰራር ስርዓት ጥናት በማድረግ በ2017 ዓ.ም ሶስት የአራር ስርዓት ጥናቶችን በኮሚሽኑ ካስጠናን በኋላ ይሄን የተጠናውን ጥናት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት፣ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር ውይይት በማድረግ ጥናቱን ተግባራዊ እንዲያደርጉም ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በዚህ ሂደት ካጠናናቸው ርዕሰ ጉዳዮች ውስጥ በጣም ወሳኝና ወቅታዊ ነው ብለን የወሰድነው ከነዳጅ ስርጭትና አቅርቦት ጋር ተያይዞ የሚመጣው ችግር ነው፡፡

በየአካባቢው የነዳጅ አቅርቦት፣ የነዳጅ አቅርቦት ስርጭት ትልቅ አሮሮ ትልቅ ጩኸት በመንግስት ተቋማትም፣ በማህበረሰቡ ውስጥም አጠቃላይ ጩኸት፣ የመልካም አስተዳደር ችግር ሲነሳበት የነበረ ነው፡፡ በመሆኑም ከክልሉ ንግድና ኢንቨስትመንት ቢሮ ጋር በመሆን ሰፊ ጥናት አስጠንተን በክልልችን ውስጥ ካሉ ሀያ ስምንት(28) የሚሆኑ የነዳጅ ማደያዎች ሀያስምንቱ ውስጥ ሀያዎች (20) ተጠንተዋል፡፡ ጥናት ካደረግነው የጥናቱን ግኝት ከባለድርሻ አካላት ጋር የጥናቱን ግኝት ምክረ-ሀሳብ ጭምር ተወያይተን ወደ መፍትሄና ስራ በመግባት ተሰርቷል፡፡ ለክልሉ መንግስት ጭምር ጥናቱን አቅርበን የጥናቱን አስፈላጊነት ላይ ተግባቦት ተፈጥሮ እዛ ውስጥ የነበሩ ግኝቶችና ምክረ ሀሳቦች ተቀባይነት አግኝተው ወደ ስራ የገባንበት ስራ ነበር፡፡

**ፀረ-ሙስና፡- ህግ የማስከበር ስራዎች ላይ ምን ተግባራት እንደተከናወኑ ቢገልጹልን?**

ም/ኮ ዳግም ዳኔኤል፡- ከሙስና መከላከል በተጨማሪ ህግ የማስከበር በሚሰራበት ግዜ ኮሚሽናችን የመከላከል ስራዎችን ይሰራል፡፡ ከመከላከል ስራ ካለፈና የሙስና ወንጀል ሆኖ ሲገኝ የመክሰስና የመመርመር ስልጣን ላለው አካል እንልካለን፡፡ በዚህ ሂደት ላይ ለመመርመርና መክሰስ ስልጣን ላለው መላክ ብቻ ግብ ሊሆን አይችልም፡፡ ኮሚሽናችን የአጠቃላይ የፀረ-ሙስና ትግሉን የመምራት፣ የማስተባበር ኃላፊነት በህግ የተጣለበት በኮሚሽኑ ላይ ነው፡፡ ስለዚህ ይሄን የበለጠ ትግሉን ጠንካራ ለማድረግ የለየናቸውን ለሚመለከታቸው የፍትህ አካላት የላክናቸውን ጉዳዮች ለክትትል እንዲመቸን ከፍትህ ቢሮ፣ ከክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን፣ ከክልሉ ዋና ኦዲተር መስሪያቤት ጋር የጋራ መግባቢያ ሰነድ ተፈራርመናል፡፡ የጋራ ፎረም መስርተናል፡፡

ይሄ ፎረም፣ የጋራ መግባቢያ ሰነድ መፈራረማችን የእኛ ኮሚሽን ለፖሊስ የተላኩ ጉዳዮች ምን ላይ እንዳሉና ምን ደረጃ ላይ ናቸው፤ አቃቢ ህግ የክስና ክርክር ሂደቱን እንዴት እየተከታተለው ነው፤ የክስና ክርክር ሂደቱ ብቻም ሳይሆን በውሳኔ አሰጣጥ የሙስና ጉዳዮች በፍርድቤት ምን ያክል ትኩረት እያገኙ ነው፤ የሚለውን ነገር ብቻም ሳይሆን ውሳኔ ከተሰጠም በኋላም ሆነ የክርክር ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ በሪፖርት ለእኛ የሚላከበትን መንገድ የጋራ ሰነድ አዘጋጅተን፣ የጋራ መግባቢያ ሰነድ ተፈራርመን ትግሉን በጋራ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር አንድ አሀድ ሆነን እየመራን ያለንበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ ይሄን ቅንጅት መፍጠራችን ደግሞ የመረጃ ቅብብሎሹ ከፍተኛ እንዲሆንና በመሀል በፊት ተንጠባጥበው ሲዘነጉ የነበሩ ጉዳዮች ጭምር የጋራ ትኩረት ያገኙበት አግባብ ስላለ እነዚህ ባለድርሻ አካላት ከሚባሉት ጋር ባለድርሻ ሳይሆኑ ሁላችንም ባለቤት መሆን በዚህ ጉዳይ ላይ ደግሞ ማድረግ ያለብንን መንፈስ በጋራ ሰርተናል፡፡ ቀጣይም አጠናክረን የምንቀጥል ይሆናል፡፡

**ፀረ-ሙስና፡- በመጨረሻ የቀረ ወይም ማስታወስ የሚፈልጉት ካለ?**

ም/ኮ ዳግም ዳኔኤል፡- ሙስናና ብልሹ አሰራር የሁሉንም ዜጋ ህወት የሚነካ ጉዳይ ነው፡፡ ለአንድ አካል፣ ለአንድ ተቋም የሚተው ጉዳይ ሳይሆን የሁሉም ባለድርሻ አካል እንደመሆኑ መጠን ሁላችንም ይመለከታል፡፡ ሁሉም ይመለከተዋልና በዚህ ጉዳይ ሁሉንም ባለድርሻ አካል ያሳተፈ ሁሉም ሚናው በተገቢው እንዲወጣ፡፡ በተለይ የሀይማኖት ተቋማት፤ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ትምህርት ተቋማት፣ ፍትህ አካላት ሁሉም በዚህ ጉዳይ ባለቤት ናቸው፡፡ ጉዳዩ ለሆነ አካል ብቻ የሚተው አይደለም፣ ሁሉም በያገባኛል ስሜት አንድ አሀድ ሆነን ተሳስበንና ተሳስረን ከሰራን ሙስናን አሁን ላለው የብልጽግና ጉዞ ስጋት ወደማይሆንበት አስከንቀለብስ ድረስ በጋራ እጅ ለእጅ ተያይዘን መስራት አለብን የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡

አመሰግናለሁ!

# ሳይቃጠል በቅጠል

የሚዲያ ተቋማት ሙስናን ለመከላከል ያላቸው ሚና

የሚዲያ ተቋማት ሙስናና ብልሹ አሰራርን በማጋለጥ ተጠያቂነትን እና ግልፅነትን ለማስፈን በትጋት መስራት ወቅቱ የሚጠይቀው አንገብጋቢ ጉዳይ ነው። ይህ አቅጣጫ በፀረ-ሙስና ትግል ውስጥ ስትራቴጂካዊ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ከውጤታማነት አኳያም ተመራጭ ሲሆን ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሚደረግ ትግል በመሆኑ ከፍተኛ ርብርብን ይጠይቃል፡፡ ምንም አይነት ልማት ማከናወን ቢቻልም ሙስናን መከላከል ካልተቻለ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት እንደማይቻል የማስተማር ሚናቸውን በጉልህ መወጣት አለባቸው፤ ከዚህ አኳያ ለሙስና መከላከል የተለየ ትኩረት ሊሰጡ ይገባል፡፡

ሌላው የሚዲያ ተቋማት ሚና ኅብረተሰቡ የተለያዩ የሙስና መከላከል ህጎችን፣ ደንቦችን፣ እና መመሪያዎችን እንዲያውቅና በዚህ ላይ በመመስረትም የህጎችና ደንቦችን በአግባቡ መተግባር እንዲከታተል ማስቻል ነው፡፡ ይህም ሙስናን በእውቀት ላይ ተመስርቶ ለመታገል እድል ይፈጥራል፡፡ ከዚህ አንጻር ህብረተሰቡ የሙስናን ምንነት፣ መንስኤውን፣ ጉዳቱንና የመከላከያ ሥልቶቹን በአግባቡ ተረድቶ የፀረ-ሙስና ትግሉ አጋር እንዲሆን የማድረግ ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ህብረተሰቡ የሙስና ድርጊትን በመጠቆም፣ ምስክርነት በመስጠት እና በሌሎች የፀረ-ሙስና ትግል ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን በማስቻል የፀረ-ሙስና ትግሉ ተከታታይነት ባለው መልኩ ትልቅ አጀንዳ ሆኖ እንዲቀጥል መሥራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

የሚዲያ ተቋማት ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለማጋለጥና ተጠያቂ ለማድረግ፣ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ፣ ግልፅነትና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚጠቀሙባቸው ስልቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

የህብረተሰቡን ተሳትፎ ማሳደግ፡- ሚዲያ ሙስና በህብረተሰብ፣ በኢኮኖሚ እና በመልካም አስተዳደር ላይ እያስከተለ ያለውን ጎጂ ተጽእኖ በማሳየት የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ ይችላል። የሚዲያ ተቋማት የሙስና ወንጀሎችን በመዘገብ፣ በዜጎች ላይ የሚያደርሰውን ተፅዕኖ በማሳየት እና ህብረተሰቡን ስለመብቱና ግዴታው በማስተማር በፀረ-ሙስና ትግሉ የማህበረሰቡን ተሳትፎ ማሳደግ ይችላሉ።

ግልጽነት እና ተጠያቂነት፡- የሚዲያ ዘገባዎች በመንግስት ተቋማት ውስጥ ግልፅነትን ማሳደግ እና የመንግስት ባለስልጣናትና ሰራተኞች ለድርጊታቸው ተጠያቂ እንዲሆኑ ያደርጋል። ሚዲያው የመንግስትን ተግባራት፣ በጀት እና የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶችን በመከታተል እና ሪፖርት በማድረግ ሙስናን ለመከላከል እና የህዝብ ሀብት በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ያስችላል። የሙስና ወንጀል ጠቋሚዎችን ምስጢር መጠበቅ፡- የሚዲያ ተቋማት የሙስና ወንጀል ጠቋሚዎችን ማንነት እንዳይገለጽ በማድረግ እና ፍርሃት እንዳይሰማቸው ሁኔታዎችን በማመቻቸት ተደብቀው ሊቆዩ ይችሉ የነበሩ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለማወቅ ይቻላል።

የፀረ-ሙስና ዘመቻዎች፡- የሚዲያ ድርጅቶች በሙስና ላይ የቅስቀሳ ዘመቻዎችን መምራት፣ የፀረ-ሙስና ተግባራትን ማስፋፋት፣ ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ ከመንግስት ተቋማት እና ከአለም አቀፍ አጋሮች ጋር በመተባበር ሙስናን በተለያዩ ደረጃዎች መከላከል ይችላሉ።

ሙያዊ ስነ ምግባርን ማክበር፡- የሚዲያ ተቋማት የሥነ ምግባር ደንቦችን በማክበር በጋዜጠኝነት ሥራ ላይ ታማኝነትን ማሳደግ እና ራሳቸው በብልሹ አሰራር ውስጥ ተባባሪ ከመሆን መቆጠብ አለባቸው። የሚዲያ ተቋማት የሥነ ምግባር ደንብን በማክበር እና የአርትዖት ነፃነትን በማረጋገጥ በአድማጭ ተመልካቾቻቸው መካከል ታማኝነትን እና መተማመንን ሊጠብቁ ይገባል።

የሚዲያ ተቋማት ሙስናን በመዋጋት ረገድ ወሳኝ ሚና የሚጫወቱት መረጃዎችን በመሰብሰብና በመለየት፣ የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ፣ ግልጽነትን በማስፈን እና የምርመራ ጋዜጠኝነትን ሥራን በማከናወን ሙስናና ብልሹ አሰራር ላይ የተሳተፉትን በማጋለጥና አጥፊዎችን ተጠያቂ በማድረግ ነው። በመሆኑም በህብረተሰቡ ውስጥ መልካም አስተዳደርን፣ ተጠያቂነትን እና ግልጽነትን ለማስፈን ነጻ እና ገለልተኛ ሚዲያ ወሳኝ ነው።

የምርመራ ጋዜጠኝነት፡- ከተለያዩ ወገኖች አቤቱታዎችን፣ ጥቆማዎችን፣ ፍንጮችን፣ ጭምጭምታዎችን መሠረት በማድረግ፣ በራሱ እየመረመረና እየተከታተለ ውስብስብና የተደበቁ እውነታዎችንና ድርጊቶችን ፈልፍሎ በማውጣት በማስረጃ እያስደገፈ ለሕዝብ ይፋ የማድረግ የጋዜጠኝነት ተግባር ነው፡፡ በዚህም ጋዜጠኞች በጥልቅ ጥናት ላይ በመመስረትና ዘገባ በመስራት ወንጀለኞችን ተጠያቂ ማድረግ ይችላሉ። በመሆኑም በሙስና የተዘፈቁ ተግባራትንና ጥፋቶችን በማጋለጥ እና በሙስና ተግባር ላይ የተሰማሩ አካላትን ተጠያቂ በማድረግ ረገድ የምርመራ ጋዜጠኞች ትልቅ ሚና ይጫወታሉ።

ሚዲያ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ጉልህ ሚና ከሚጫወትባቸው ዘዴዎች መካከል የምርመራ ጋዜጠኝነት አንዱ ሲሆን፣ በምርመራ ጋዜጠኝነት አማካኝነት ከተለያዩ ወገኖች ሙስናና ብልሹ አሰራር ነክ የሆኑ አቤቱታዎችን፣ ጥቆማዎችን፣ ፍንጮችን፣ ጭምጭምታዎችን መሠረት በማድረግ እየመረመሩና እየተከታተሉ የተደበቁ እውነታዎችንና ድርጊቶችን ፈልፍሎ በማውጣት በመረጃ እና በማስረጃ እያስደገፉ ለሕዝብ ይፋ ማድረግም ሌላኛው የሚዲያ ሚና በመሆኑ ይህንኑ በአግባበቡና በቁርጠኝነት መወጣት ይጠበቃል፡፡

## የ2017 አገራዊ የሙስና መከላከል ጥናት አፈጻጸም ሪፖርት

| ተ.ቁ | ተቋም | አፈጻጸም |
|---|---|---|
| 1. | የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 5 |
| 2. | የኦሮሚያ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 24 |
| 3. | የአማራ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 10 |
| 4. | የአዲስ አበባ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 35 |
| 5. | የሶማሌ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 6 |
| 6. | የሐረሪ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 4 |
| 7. | የሲዳማ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 13 |
| 8. | የቤ/ጉ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 2 |
| 9. | የደቡብ ም/ኢትዮጵያ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 3 |
| 10. | የጋምቤላ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 0 |
| 11. | የትግራይ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 6 |
| 12. | የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 3 |
| 13. | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 12 |
| 14. | የድሬዳዋ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 2 |
| 15. | የአፋር ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 2 |
| | ድምር | 127 |

N C R S
ለ ጥ ቆ ማ
APP





# ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር

ይህ አምድ በዋናነት ትኩረት የሚያደረገው ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የማይገባ ጥቅም ለራሱ በማስገኘት ወይም ለሌላ ሰው በማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት በማድረስ በተሰጠዉ ኃላፊነት ከሌላ ሰው ላይ ጥቅም የተቀበለ ወይም የጠየቀ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም በማስገኘት የተሰጠዉን ስልጣን ወይም የህዝብ አደራ ያላአግባብ የተገለገለ፤ ወይም ለሌላ ሰው ያስገኘ ወይም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት እንዲደርስ በማድረግ ለመንግስት ወይም ለህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ የማይገባ ጥቅም የሰጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ፤ ወይም በአግባቡ ለተፈጸመ የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት ልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ስራ የማይገባ ጥቅም ለማንኛውም ሰዉ የሰጠ ወይም ከማንኛዉም የመንግስት ወይም ህዝባዉ ድርጅት ሰራተኛ የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ፈጻሚነት ተጠያቂ በመሆን በምርመራ የሙስና ወንጀል ፈፅመው የተገኙ አካላት መረጃዎችን ለአንባቢያን ተደራሽ የምዳረግበት ነው።

ከሳሽ የጋሞ ዞን ፍትህ መምሪያ የሙስና ክስ ወንጀል ዐቃቤ ሕግ በተከሳሽ መስፍን መርደክዮስ ላይ በክስ መዝገብ ቁጥር 51672 በቀን 13/02/2017 ክስ አቅርቧል።

ተከሳሽ የተለያዩ የአርባምንጭ ከተማ ነዋሪ የሆኑ ግለሰቦችን በህገ ወጥ መንገድ የያዛችሁትን ቦታ ወደ ህጋዊነት አስቀይራለሁ እኔ የአርባምንጭ ከተማ ካዳስተር ኃላፊ ነኝ በማለት ከ500 ሺህ ብር በላይ ከተቀበላቸው በኋላ ሀሰተኛ የሰነድ ማስረጃ ሰጥቷቸዋል።

በመሆኑም ተከሳሽ የሙስና ወንጀልን ለመከላከል የወጣውን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 23 እና 32 በመተላለፍ ሀሰተኛ ሰነድ ማስረጃና አታላይነት ፈፅሟል በሚል ለጋሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰውና በሰነድ ማስረጃ ያስረዳ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ተከሳሽ በቀረበበት ክስ ራሱን እንዲከላከል ብይን ሰጥቶ ተከሳሽም የበኩሉን መከላከያ በማቅረብ ሲከራከሩ ቆይተዋል።

በሂደቱም የጋሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሽ በግለሰቦች ላይ የፈፀመውን የአታላይነት ወንጀል መከላከል ባለመቻሉ ጥፍተኛ በማለት በቀን 08/11/2017 ዓ.ም በዋለው ችሎት በአስር ዓመት ፅኑ እስራትና በ13ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ሲል ወስኗል።

## የ2017 በጀት ዓመት አገራዊ የሙስና ጥቆማ መረጃ

| ተ/ቁ | ተቋም | የቀረበ ጥቆማ ብዛት | በአስቸኳይ ሙስና መከላከል የታየ | ለምርመራ የተላከ | የሙስና መከላከል ምክር አገልግሎት የተሰጠበት | ሌሎች |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የፌደራል ሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 473 | 24 | 145 | 111 | 46 |
| 2. | የጋምቤላ ሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 15 | 5 | 4 | 6 | - |
| 3. | የድሬዳዋ ሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 35 | 2 | - | 2 | 31 |
| 4. | የሲዳማ ክልል ሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 472 | 46 | 47 | 14 | 365 |
| 5. | የትግራይ ክልል ሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 621 | 6 | 469 | 128 | 18 |
| 6. | የደቡብ ኢት/ክልል ሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 81 | 59 | 17 | 22 | 17 |
| 7. | የሶማሌ ክልል ሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 404 | 64 | 193 | 72 | 75 |
| 8. | የኦሮሚያ ክልል ሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 281 | 99 | 88 | 94 | - |
| 9. | የአማራ ክልል ሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 796 | 73 | 227 | 390 | 106 |
| 10. | የሀረሪ ክልል ሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 54 | 8 | 9 | 5 | 32 |
| 11. | የአዲስ አበባ ሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 2022 | | 105 | 1231 | 686 |
| 12. | የቤ/ጉምዝ ክልል ሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 8 | - | - | - | - |
| 13. | የአፋር ክልል ሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 22 | 6 | - | - | - |
| 14. | የደ/ም/ኢት/ ክልል ሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 729 | 292 | 124 | 16 | 297 |
| 15. | የማዕከላዊ ኢት/ ክልል ሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን | 822 | 687 | 133 | 2 | - |
| | አጠቃላይ ድምር | 6835 | 1371 | 1561 | 2093 | 1673 |

NCRS App